ሰላም ጤና ይስጥልኝ የሳምንታዊ የዜና ዘገባ አድማጮቻችን እንደምን ሰንብታችሁዋል:: ዛሬም እንደተለመደው ሁሉ በቅድሚያ ርዕሶቹን እናስቀድማለን:-

በወያኔ ባለስልጣናት መካከል ከፍተኛ ብጥብጥ መፈጠሩ ተጋለጠ፤

ተፈራ ዋልዋ እና መለስ በጉባኤው አዳራሽ ውስጥ እሰጥ አገባ ገጠሙ፤

ከ72 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ አባክኖዋል በሚል የመለስ ቅርብ የሆኑ ደህንነቶች በተፈራ ላይ ማስረጃ እያሰባሰቡ ነው ተባለ፤

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊና የሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ በምስጢር የተናጠል ድርድር መጀመራቸው ተነገረ፤

የወያኔ ባለስልጣናት ስለድርድሩ እንደማያውቁ ተጠቆመ ፤

አደራዳሪዎቹ ከፍተኛ የተ.መ.ድ. ዲፕሎማቶች ናቸው ተባለ፤

ከፍተኛ የራሺያ ወታደራዊ መኮንኖች ከወያኔ ባለስልጣናትና ጄኔራሎች ጋር ምስጥራዊ ውይይት አደረጉ፤

በጅጅጋ ከተማ በፈነዳ ፈንጅ 5 ሰዎች ሲሞቱ ከ20 በላይ ቆሰሉ፤

በርካታ የጅጅጋ ነዋሪዎች ታፍሰው ካምፕ ውስጥ ታጎሩ፤

በየወረዳው በካድሬነት ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ወያኔዎች ለዩኒቨርስቲ መምህርነት ተመደቡ-አዲዮስ ትምህርት፤

የወያኔ ተሌቭዥን ባለስልጣናት በጥቅም ተጋጩ

የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል አብረን እንከታተል:-

EthioLion.com

የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት መካከል የተከሰተው ያለ መግባባት ቀስ በቀስ ወደ አደባባይ እየወጣ መሆኑን ከተለያዩ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገለጠ::

በከፍተኛ መኮንኖች መካከል የተጀመረው ሽኩቻ አንዴ ጋብ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጋል እያለ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን የሆነው ተፈራ ዋልዋ እና በመለስ ዜናዊ መካከል በስብሰባ አዳራሽ ውስጥ እርስ በርስ ከመነታረካቸውም በተጨማሪ በጋዜጣ ላይ ሳይቀር ተቃውሞ ማሰማት መጀመራቸው ታውቋዋል::

በወያኔዎቹ ባለስልጣናት መካከል የተከሰተው ይኸው ልዩነት ውስጥ ወስጡን ሲብላላ የቆየ ቢሆንም አሁን ግን በይፋ እስከ መቃወም እና ማውገዝ ደረጃ ላይ መድረሱን የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቶዋል::

ለሁለቱ ባለስልጣናት ልዩነት ዋነኛ መንስኤ ነው የተባለው የወያኔ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ጥቂት ቀናት በፊት በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ የድሬደዋንና የአዲስ አበባን ወጣት ፎረም አባላትን አወቃቀር በተመለከተ የማዕከላዊ ኮሚተዎቹ ተሰብስበው ውይይት ባደረጉበትና ከ180 ማዕከላዊ ኮሚተ አባላት መካከል ተፈራ ዋልዋ ብቻ ባቁዋም ተለይቶ የመለስን ሀሳብ በይፋ ውድቅ በማድረጉ በሁለቱ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት መካከል ፍጥጫው አይሎ መምጣቱና ይህንኑ ፍጥጫ ተከትሎ በመለስ ውስጣዊ ትዕዛዝ ከብአዴን ምክትል ሊቀመንበርነቱ እንዲነሳ መደረጉን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

በዚሁ ግማሽ ቀን በፈጀው ስብሰባ ላይ ለቀጣይ አመታቶች ስልጣናቸውን ያለ ተቀናቃኝ አስጠብቀው የሚቆዩበትን እቅድ በተለይም ወጣቱን ሀይል ለመያዝ በነደፉት መሰረት የወጣት ፎረም ተጠሪነቱ ለመለስ እንዲሆንና የተሰጣቸውን የፖለቲካ ስራ እንዲያከናውኑ የሚያስገድድ «የወጣት ሊጎቹ የኢህአዴግን አወቃቀር የሚከተሉ መሆን አለበት » በማለት መለስ ያቀረበውን ሀሳብ ተፈራ ዋልዋ ሙሉ በሙሉ በመቃወም አቁዋም መውሰዱን ዘገባው ገልፆ « ወጣቶቹ በመረጡት አወቃቀር መደራጀት አለባቸው » በማለት ድፍረት የተቀላቀለበት ንግግር በማሰማቱ በአዳራሽ ውስጥ የነበሩት ከፍተኛ ባለስልጣናት ጭምር በድንጋጤ ጭንቅላታቸውን ይዘው በአግራሞት ሲያወዛውዙ እንደነበረም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

በተለይም ተፈራ ዋልዋ «እስከ ዛሬ የሄድንባቸው መንገዶች ትክክል አለመሆኑን ባገኘናቸው ውጤት የምናውቀው ስለሆነ አሁንም ይህንኑ ተግባር መድገም የለብንም »በማለት ሀይለ ቃል ጭምር በመሰንዘሩ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩት የማዕከላዊ ኮሚተ አባላት ከመደንገጣቸውም በላይ በተፈራ ቅፀበታዊ ለውጥ ግራ የተጋባው መለስም የሚይዘውና የሚጨብጠው ጠፍቶት «ይህ ሀሳብ ከአንድ ማዕከላዊ ኮሚተ አባል ነኝ

EthioLion.com

ከሚል ግለሰብ የማይጠበቅ ነው:: በመሆኑም የአንድ ግለሰብ አስተያየት ስለሆነ በድምፅ ብልጫ ልንወስን ይገባናል » በማለት ተሰብሳቢ ሆድ አደሮችን አስፈራርቶ ያስወሰነ ቢሆንም በመለስና በተፈራ መካከል የተጀመረው አተካሮና ጭቅጭቅ ቀጥሎበት እንዳለም ዘገባው አስረድቶዋል::

ይህ ስብሰባ ከጠተናቀቀ ከጥቂት ቀናት በሁዋላ ሕወሀት በመቀሌ ፣ ብአዴን በባህር ዳር ፣ ኦህዴድ በአርሲ እና ደኢህዴን ደግሞ በወላይታ ሶዶ ከተማ የተናጠል ጉባኤ ያደረጉ ሲሆን የሌሎቹ ተቀፅላ ፓርቲዎች የነበሩትን የድርጅት መሪዎች ባሉበት እንዲቀጥሉ ሲወስኑ ብአዴን ግን በመለስ ስውር ትዕዛዝ ተፈራ ዋልዋ ከምክትል ሊቀመንበርነቱ እንዲነሳ መደረጉን ከዘገባው ለመረዳት ተችሎዋል:: በወቅቱ ተፈራ ዋልዋ ከምክትል ሊቀመንበርነቱ እንዲነሳ መለስ ለአዲሱ ለገሰ በሰጠው ምስጢራዊ ትዕዛዝ ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም በስብሰባ አዳራሹ ውስጥ ግን አዲሱን ፈታኝ የተባሉ ችግሮች ገጥመውት እንደነበረ የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ከመስከረም 5 እስከ መስከረም 7 ቀን 2001 ዓ. ም. ለ3 ቀናት በአዋሳ በተደረገው ጉባኤ ላይም የተለየ አቋዋም ይዞ ሲከራከር የቆየው ተፈራ ዋልዋ ከወትሮው በተለየ መልኩ ከመለስ ጋር ሙግት በመግጠሙ የተነሳ ከፍተኛ ባለስልጣናቱ ተደናገግጠው ከንፈራቸውን በእጃቸው ሸፍነው፤አንገታቸውን ወደ መሬት ደፍተው ቀና ብለው ለማየት እንኩዋን ወኔ አጥተው እንደነበር የገለፁት ምንጮች እስከዛሬ ድረስ ከወያኔው መሪ መለስ ጋር ፊት ለፊት ሙግት የገጠመ ባለመኖሩ የተፈራ ወኔ አግኝቶ ፊት ለፊት አተካሮ መግጠሙ እንደ ትልቅ ጀብዱ ቆጥረው ሲሽማቀቁ እንደነበረም ምንጮቹ አስረድተዋል::

በአዋሳው ጉባኤ ላይ ተፈራ «የጠቅላይ ሚኒስትርነት ጊዜ ገደብ ሊቀመጥለት ይገባል፤ሌሎችም ቢሆን በቦታቸው ላይ የጊዜ ገደብ ሊጣልበትና ህግ ሊወጣለት አስፈላጊ ነው »በማለት ጠንካራ አቋዋም ይዞ ሲከራከር ሌሎች አዲስ እና ወጣት ናቸው የተባሉ አፍለኛ ካድሬዎች የተፈራን አቋዋም በመደገፍ ከፍተኛና የሰላ ትችት ሲያቀርቡ እነአዲሱ ለገሰና በረከት ስምኦን ግን ተፈራ ያቀረበውንና ወጣት ካድሬዎች የተቹትን ሀሳብ በመረባረብ ለአለቃቸው ታማኝነታቸውን ሲገልፁ እንደነበረ የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ከብአዴን ምክትል ሊቀመንበርነት የተነሳው ተፈራ ዋልዋ ከታምራት ላይኔ ጋር ኢህዴን በሁዋላ ብአዴን የተባለውን የወያኔ ተቀፅላ ድርጅት ሲመራ እንደነበርና ከመለስ ጋር በገባው እሰጥ አገባ ምክንያት ከስልጣኑ ሊባረር የቻለ ሲሆን፤ ሰሞኑን ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ጊዜ የፈፀማቸው የገንዘብ ምዝበራ አለ በሚል ቆሻሻ ውስጥ ተጥለው የነበሩትን ፋይሎች ለመለስ ቀኝ እጅ ናቸው የተባሉ

የደህንነት ሹማምንቶች እያገላበጡ መሆናቸው ሰውየውን ወደ ዘብጥያ ለማውረድ ሳይታሰብ እንዳልቀረ ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራን ስጋታቸውን ገልፀዋል::

ሌሎች ወገኖች ደግሞ አሁን በወያኔ ውስጥ ብዙ ችግሮች ስላሉ ተፈራን ከማባረር ይልቅ አባብሎ ማሰራት ግድ ስለሚል መለስ የከፋ እርምጃ ሊወስድበት አይችልም ሲሉ የበኩላቸውን አስተያየት ሲሰጡ ተደምጠዋል::

በተለይም አምና በ2000 ዓ. ም. የአውሮፓ ህብረት ተፈራ ዋልዋ ለሚመራው የአቅም ግንባታ መስሪያ ቤት በእርዳታ ከ6 ሚሊዮን ዩሮ ወይም 72 ሚሊዮን ብር በላይ አስረክቦት እንደነበርና ገንዘቡ ምን ላይ እንደዋለ አስከ ዛሬ ድረስ ሳይጠይቁት ቆይተው አሁን ከመለስ ጋር ውዝግብ ውስጥ ሲገባ ጊዜ ጠብቀው ይህንኑ ፋልና ሌሎችንም ወደ ሁዋላ ተመልሰው እያገላበጡ ሊወነጅሉት እንደሚችሉ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ወጣቶች ሀሳባቸውን በነፃነት እና እነሱ በፈለጉት መንገድ ተዋቅረው ይግለፁ፤ በማለት የወጣቱን ካድሬዎች ቀልብ ለመሳብ ደፋ ቀና እያለ የሚውተረተረው ተፈራ ከወትሮው በተለየ መልኩ ጥያቄ በማንሳቱ የተነሳ በመለስና በነአዲሱ ጥርስ የተነከሰበት ከመሆኑም ባሻገር ከወትሮ ከሚያደርጉት ማህበራዊ ህይወት እንቅስቃሴ ሁሉ ያገለሉት መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አብራርቶዋል::

አንዴ ጥርስ የነከሰበትን ጊዜ ጠብቆ ማጥቃት የሚችልበት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከዚህ በፊት በታምራት ላይኔ ፤በስዬ አብርሀ ላይ መውሰድ የጀመረውን እርምጃ አጠናክሮ ቀጥሎበት አሁን ደግሞ በሽፈራው ጃርሶ እና በተፈራ ዋልዋ ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

መለስ ዜናዊ በመላ ሀገሪቱና በህዝቡዋ ላይ እየሰራ ያለውን ሸፍጥ አሁንም ይበልጥ ቀጥሎበት እንደሚገኝ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

ወያኔና ሻዕቢያ በፈጠሩት የእርስ በርስ ሽኩቻ ምክንያት ከ80 ሺህ በላይ ለሞት የተዳረጉበት የባድመ ውጊያ በነመነለስና ስዩም መስፍን በሰሩት ተንኮል የአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለሻዕቢያ የወሰነ ሲሆን ይህንኑ ትዕዛዝ ኣላከብርም ሲል የቀየው መለስ ሰሞኑን በምስጢር ከሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ድርድር መጀመሩን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል::

ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተወከሉ ከፍተኛ ዲፕሎማቶች ያሉበት ነው የተባለው ይኸው ምስጢራዊ በሆነ መልኩ መለስንና ኢሳያስን እያደራደሩ ነው ያሉት ውስጥ አዋቂ ምንጮች በተናጠል አንዴ አዲስ አበባ ሌላ ጊዜ አስመራ በማለት

ሲንከራተቱ እንደነበርና ቀጣይ የተናጠል ምስጥራዊ ድርድር በቅርቡ እንደሚደረግ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

« ሀገርህ ተወረረ፤ ድንበርህ ተደፈረ ፤ተነስ ፤ታጠቅ ፤ዝመት » ብሎ ከ80 ሺህ በላይ የኢትዮጵያን ወጣቶች ያስፈጀው  መለስ ዜናዊ ከጄኔራል ሳሞራ የኑስ በስተቀር አንድም ባለስልጣን ሳይሰማና ሳያውቅ ሰሞኑን በምስጢር ከሻዕቢያው መሪ ጋር ምስጢራዊ  የተናጠል ድርድር ጀምረዋል መባሉ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ይህ ግለሰብ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ እየሰራ ያለው ሸፍጥ አሁንም እንዳላቆመ የሚያመላክት ነው ሲሉም ምንጮቹ ገልፀዋል::

ሀገሪቱዋን ወደብ አልባ አድርጎ ለሻዕያ ያስረከበው መለስ የራሴ ናቸው የሚላቸውን ባለስልጣናት እንኩዋን ሳያማክር በድብቅ በተ. መ. ድ. ከፍተኛ ዲፕሎማቶች በኩል የተናጠል ድርድር መጀመሩ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ብቻ ሳይሆን አስከ ዛሬ ከፈፀማቸው ወንጀሎች በላይ አሁንም እየሰራ መሆኑን ያሳያል የሚሉ ወገኖች በርካቶች ናቸው::

ታፍራና ተከብራ የኖረቻውን ሀገራችንን መለስ ዜናዊ  ወደብ አልባ አድርጎ የብጥስጣሽ ሀገር ደጅ ጠኚ እንድንሆን ማድረጉ ሳያንስ አሁን ደግሞ ከሻዕቢያው መሪ ጋር ምስጢራዊ ድርድር መጀመሩ የኢትዮጵያን ህዝብ ህልውና ጥያቄ ውስጥ ሊከት እንደሆነም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ከሻዕቢያ ጋር ድርድር የጀመረው መለስ በባለስልጣናቱ ላይ እምነት እያጣ በመምጣቱ በምስጢር እና በድብቅ የቀድሞ ወዳጁ ጋር ድርድር ማድረጉ ወትሮም ከግለሰቡ ባህሪይ አንፃር የወሰደው እርምጃ የሚጠበቅ ነው ሲሉ ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል::

የራሺያ ከፍተኛ ወታደራዊ  መኮንኖች ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ ከወያኔ ባለስልጣናትና ጄኔራሎች ጋር በምስጢር መወያየታቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

ከረጅም ዘመን በሁዋላ በወታደራዊ ግንኙነት ወዳጅነት ለመፍጠር ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖቹዋን  ስትልክ የመጀመሪያ ጊዜ እንደሆነ የገለፁት ምንጮቹ በምስራቅ አፍሪካ በኩል የተለያዩ የምዕራብ ሀገራት ጦራቸውን በማስፈራቸው የተነሳ ስጋት የገባት ራሺያ በአሁኑ ሰዓትም ከአሜሪካ ጋርም ያላት ግንኙነት እየሻከረ በመምጣቱ ምክንያት የራስዋን  ወታደራዊ ኃይል በአካባቢው  ለማስፈር እንዲያመቻት ከወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት እና ጄኔራሎች ጋር ምስጢራዊ ውይይት ማድረጋቸውን ምንጮች ገልፀዋል::

አሜሪካ  በአሁን ሰዓት ፕሬዝደንታዊ ምርጫ ላይ ስለሆነች በተለይም ኦባማ ሊመረጥ ይችላል የሚል ስጋት ውስጥ የወደቁት የወያኔ ባለስልጣናት ከራሺያ ጋር ቀድመው ውስጥ ውስጡን ድርድር መጀመራቸውን የገለፁት ምንጮቹ ወያኔዎች ከራሺያ ጋር የጀመሩትን ምስጥራዊ  ውይይት   አሜሪካኖች ሰምተው እንዳያኮርፉ መለስ ዜናዊ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስብሰባ ላይ ከነ ቡሽ ጋር በተገናኙበት ወቅት ታቅዶ የተደረገ መሆኑንም ምንጮቹ አስረድተዋል::

በደርግ ዘመነ  መንግስት ጊዜ ራሺያ በኢትዮጵያ ወታደራዊ ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራት በመሆኑ በአሁን ወቅት ምስራቅ ኢትዮጵያ ኦጋዴን ውስጥ ቻይና እየዳከረችበት ያለውን የነዳጅ ቦታ ራሺዎች በ1970 ዎቹ ውስጥ ትልቅ ደረጃ አድርሰውት እንደነበረ የሚያውቁት ወያኔዎች እግረ መንገዳቸውንም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ምስጥራዊ ውይይት ሳያደርጉ እንዳልቀረም ምንጮቹ አብራርተዋል::

የራሺያ ወታደራዊ አታሺዎች ለአንድ ሳምንት በአዲስ አበባ የመከላከያ ዋና ቢሮና የደብረ ዘይት አየር ኃይል  ካምፑን  እና ሌሎችንም ወታደራዊ ተቋማት ተዘዋውረው ከመመልከታቸውም በላይ ምስጢራዊ ድርድር ያደረጉ ሲሆን በተለይም ኦባማ  ከተመረጠ በኢትዮጵያ ላይ ያለንን ፖሊሲ ለውጥ እናደርጋለን በማለት ሴናተር ዶናልድ ፔይን በመግለፃቸው የተደናገጡት የወያኔ ባለስልጣናት አስቀድመው ከራሺያ ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር እና ለመጣበቅ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል::

የወያኔ ቡድን በአሁኑ ወቅት  በውስጣቸው ከፍተኛ ሽኩቻ ስላለና የአሜሪካም ሁኔታ ስላላስተማመናቸው እነ መለስ በምስጢር ከራሺያ ጋር ለመለጠፍ እየተጣደፉ ነው ሲሉም ምንጮቹ አብራርተዋል::

በሌላ ዜና በጅጅጋ ከተማ መስከረም 15 ቀን 2001 ዓ. ም. ከጡዋቱ 4  ሰዓት ላይ አንድነት ሆተል ተብሎ በሚጠራው ፊት ለፊት ፈንጂ ፈንድቶ 5 ሰዎች ወዲያውኑ ሲሞቱ ሌሎች ከ20 በላይ የሚሆኑት ደግሞ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ነዋሪዎቹ የተለመደ የዕለት ጉርሳቸውን ለመሙላት ደፋ ቀና ሲሉ  ሳይታሰብ በደረሰው በዚሁ አሰቃቂ አደጋ ላይ አምስት ሰዎች የሞቱ ቢሆንም ምናልባትም ከቆሰሉት ውስጥ ሌሎች የሞቱ ሳይኖሩ እንዳልቀረ የደረሰን ዘገባ ገልፆ ጥቃቱን ያደረሰ አካል እስካሁን አለመታወቁንም ጨምሮ አስረድቶዋል::

ይህንኑ ጥቃት ተከትሎ የወያኔ ባለስልጣናት በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ስርዓቱን ይቃወማሉ አይደግፉም  ተብለው የሚጠረጠሩትን ሰዎች እያፈሱ ወደ ጦር ካምፕ እያጎሩዋቸው መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ወያኔ የአይናቸው ቀለም አላማረንም በማለት ያሻውን ሲገድል፤ ያሻውን ሲያስርና ሲያሰቃይ የነበረ ቡድን ሲሆን፤ አሁንም

ለምን ለኔ አላጎበደዱም በሚል ብቻ ምንም ከፍንዳታው ጋር ግንኙነት የሌላቸውን የጅጅጋ ከተማ ነዋሪዎች እያፈሰ ወደ ጦር ካምፕ እያጎራቸው ከመሆኑም ባሻገር ዘመዶቻቸው እንዳይጠይቋቸው መደረጉንም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ በጅጅጋ ከተማ ፍንዳታ ደርሶ በርካታ ዜጎች ምንም ባልሰሩት ጥፋት ፍንዳታውን ያደረሳችሁት እናንተ ናችሁ በማለት ከሁለት ዓመት በላይ ያለምንም ክስ አስረዋቸው ከቆየ በሁዋላ ተዘዋዋሪ ችሎት የተባለው የወያኔ ዳኞች የተሰየሙበት ፍርድ ቤት በዝቅተኛ ዋስትና የለቀቃቸው ቢሆንም የወያኔ ደህንነቶች አስረኞቹ ከእስር ቤት ሲወጡ ከበር ላይ እያፈሱ ወደ ዝዋይ እስር ቤት አዛውረው ያሰሩዋቸው መሆኑንና በአሁን ሰዓትም ያለ አንዳች ጥያቄ በዚያው እንደሚገኙ ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

እድሜውን ለማርዘም ቀና ደፋ የሚለው የወያኔ ቡድን የጀመረውን የትምህርት ተቁዋማት ማዳከም ዘንድሮ ከመቸውም ጊዜ በላይ አጠናክሮ እንደቀጠለበት ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ከዚህ ቀደም ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች እና ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁና በካድሬነት ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩትን ዘንድሮ ለዩኒቨርስቲ መምህርነት ተመልምለው ወደ ስራ ላይ ያሰማሩዋቸው መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በየወረዳው ውስጥ የካድሬነት ስራ ሲሰሩ የነበሩትና ምንም አይነት የማስተማር ልምድና ክህሎት የሌላቸውንና እንደ ጋሪ ፈረስ በአንድ በኩል የተጋረደባቸውን ከያሉበት እየለቃቀሙ እንዲያስተምሩ የቅጥር ፎርም ያስሞሉዋቸው ሲሆን ግማሾቹም ማስተማር መጀመራቸውን የገለፀው ዘገባ በዩኒቨርስቲ ውሰጥ ያሉትን ተማሪዎች በካድሬነት ለመጥመቅ እና ምናልባትም ለማመፅ ሲያስቡ አስቀድመው ለማኮላሸት ይረዳሉ ተብሎ ሳይሆን እንዳልቀረም አስረድቶዋል::

ምንም ዓይነት የማስተማር ልምድ የሌላቸው ከመሆኑም ባሻገር ዕውቀት የሌላቸው ሰዎችን ከሜዳ ላይ ሰብስቦ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አስተማሪ አድርጎ ማስገባት የወያኔን ቡድን የሚቃወሙትን ነባር መምህራንን ለመቆጣጠርና ለመሰለል ካልሆነ በስተቀር ችሎታ ኖሮዋቸው ያስተምራሉ ብዬ በፍፁም አላስብም ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ትምህርት ገዳይ የሆነ ፖሊሲያቸውን ሲቀርፁ ከፍተኛ ተቃውሞ ስናሰማ ነበር:: እነሱ ያልነው ካልሆነ ብለው ተግባራዊ ያደረጉት ፖሊሲ ተማሪውን ለቦዘኔነት ዳርገውት በየመንገዱ ላይ ሲንከራተት ማየት የሚያሳዝን ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል::

ሌላው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት በበኩላቸው ትምህርት ገዳይ ፖሊሲያቸው ወጣቱን ለስራ አጥነት የዳረገው ከመሆኑም በተጨማሪ በራሳቸው ጥረት ወደ ዩኒቨርስቲ የገቡትን ተማሪዎች የእውቀት ደሀ ለማድረግና የወያኔ አፋሽ አጎንባሽ አድርጎ ለማስቀረት ሲባል ብቻ ምንም የማስተማር ልምድና እውቀት የሌላቸውን ካድሬዎች አስተምሩ ብሎ በአዋሳ ፤በአለማያ ፤በጅማ እና በሌሎችም ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ መመደባቸው ትምህርት በኢትዮጵያ ደቅቆና ኮስሶ እንዲቀር በቀጣዩ ትውልድ ምሁር የሚባል እንዳይኖር ለማድረግ የተሸረበ ሴራ ነው ሲሉም እልህና ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት ሲገልፅ ተደምጠዋል::

በአሁን ሰዓት በወያኔ የትምህርት ፖሊሲ ምክንያት በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ስራ ፈት ሆነው በየመንገዱ ላይ ሲንከራተቱ ወያኔዎች መልሰው አደገኛ ቦዘኔ እያሉ አፍሰው ወደ ዝዋይና ሸዋ ሮቢት እስር ቤት እያጎሩዋቸው በርሀብና በችጋር እያሰቃዩዋቸው መሆኑን እና አሁንም የተማረ ሳይሆን የዩኒቨርስቲ በር ረግጦ የወጣ ትውልድ ለማፍራት እና ይህንን የመሰለ አሳፋሪና አሳዛኝ ትውልድ ገዳይ የሆኑ ካድሬዎችን መድቦ አስተምሩ ማለት መቀለድ እንደሆነ ምሁራኖች በንዴት ይገልፃሉ::

በመጨረሻም የወያኔ ቡድን እስከ ዛሬ ከአንድ ማሰራጫ ጣቢያ ሲያስተላልፍ የነበረውን ተሌቭዥን ኢትዮጵያዊነት በህዝብ ውስጥ እንዳይኖር ለማድረግ በጎጥና በመንደር ለመከፋፈል ሲል ብቻ ለአራቱም የብሔር ድርጅቶች ከፋፍሎ መስጠቱን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ::

ቀድሞ ከዋናው አዲስ አበባ ይተላለፍ የነበረው የአማርኛ፤ የኦሮሚኛ እና የትግርኛ ፕሮግራም የሰዓት ክፍፍል ተሰጥቶዋቸው ሲተላለፉ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ግን ለኦሮሚኛ ፤ለትግሪኛ፤ ለደቡብና ለአማራ በአማርኛ ፕሮግራም ለአራቱም ድርጅቶች ከፋፍለው የአየር ሰዓት መሸጡን ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገልፀዋል::

ለህወሀት -መቀሌ ፤ለብአዴን -ባህር ዳር ፤ ለኦህዴድ -ናዝሬት ላይና ለደቡብ አዋሳ ላይ ሆነው ፕሮግራማቸውን እንዲያስተላልፉ ከዋናው ተሌቭዥን ማሰራጫ ጋር የተስማሙ እና የተፈራረሙ ቢሆንም ሰሞኑን ከማስታወቂያ ጋር በተያያዘ በክልሎችና በዋናው ተሌቭዥን ባለስልጣናት መካከል ግጭት መፈጠሩን ምንጮቹ ገልፀዋል::

በተለይም የኦሮሚኛ ፕሮግራም ዝግጅት ክፍሎች በራሳቸው ጥረት ለፍተውና ደክመው ያገኙትን ማስታወቂያ የዋናው ተሌቭዥን ስራ አስኪያጅ ሆኖ በቅርቡ ከወይን ድምፅ ተዛወሮ የመጣው ብርሀን የተባለው የወያኔ ካድሬ ኮሚሽን ክፈሉን በማለት ትዕዛዝ ያስተላለፈ ቢሆንም የኦሮሚኛ ፕሮግራም አዘጋጅ ካድሬዎች በበኩላቸው የአየር ሰዓቱን ሙሉ በሙሉ ክፍያ ፈፅመን የገዛናችሁ በመሆኑ አንከፍልም በማለት ግጭት መፍጠራቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል::

EthioLion.com

በአንፃሩ ደግሞ የትግሪኛ ፕሮግራም የሆነው የህወሀት ክፍለ ጊዜ የሚሰራውን ማስታወቂያ ክፍያ ሳይከፍልበት እና ሳይጠየቅ እየሰራ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው ዞሮ ዞሮ ወያኔ እየሰራ ያለው የሀገሪቱዋ ህዝቦች ባህላቸውንና ታሪካቸውን ጠንቅቀው እንዳያውቁ ፤ ሆን ተብሎ የመንደር አስተሳሰብ ይዞ እንዲቀር ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው ሲሉ ምን ጮቹ አብራርተዋል።

EthioLion.Com